?? ????? ? ?? ? ? ?? ?? ? ????

ልሳነ ህግጋዘጣ

**Benishanigul Gumuze Regional State**

**LISSANE HIG GAZETA**

23 ኛ ዓመት ቁጥር 143
የካቲት /2009

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊመንግሥት ክልል ምክር ቤትጠባቂነት የወጣ አዋጅ**

23th Year No 143
February /2017

---

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር143/2009 ዓ.ም

**<u>አዋጅ ቁጥር143/2009 ዓ.ም</u>**

**<u>የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር</u>**

**<u>ለመወሰን የወጣ አዋጅ</u>**

---

<u>አዋጅ ቁጥር143/2009 ዓ.ም</u>

<u>የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር</u>

<u>ለመወሰን የወጣ አዋጅ</u>

የክልላችን የኢኮኖሚ ዕድገት ከደረሰበት ደረጃ ጋር የተጣጣመ እና የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያግዝ ዘመናዊ፣ቀላልና ቀልጣፋ የግብር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የግብር አከፋፈል ሥርዓቱ ፍትሀዊነት ያለው እንዲሆን እና ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች በግብር መረብ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ሕገ-መንግስት

አንቀጽ 49 ንኡስ አንቀጽ /3/1 እና 11 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

**አንቀጽ 1. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 143/2009 ዓ.ም. ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**<u>PROCLAMATION NO. 143/2017</u>**

<u>THE BENISHANGUL-GUMUZ REGIONAL STATE **INCOME TAX PROCLAMATION**</u>

---

**<u>PROCLAMATION NO. 143/2017</u>**

<u>THE BENISHANGUL-GUMUZ REGIONAL STATE **INCOME TAX PROCLAMATION**</u>

WHERE AS, it has become necessary to introduce modern, simple and efficient tax system that supports the economic development and which is in accord with the level of economic developemt achieved so far.

WHERE AS, it is found essential to make the tax system fair and bring income that are so far not subject to tax into the tax net,

NOW, THEREFORE, in accordance with the powers vested under Article 49 sub article /3/ 1/ and 11 of the revised constitution of the Benisshangul-Gumuz Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

**<u>PART ONE</u>**

**<u>GENERAL</u>**

**Article 1.<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the

"The Benishangul- Gumuz Regional State Income Tax Proclamation No.143/2017 "

**Article 2.<u>Definitions</u>**

A term used in this Proclamation that is defined in the Regional Tax Administration

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጁ ትርጉም የተሰጠው በዚህ አዋጅ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ አዋጅ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

1) "የገንዘብ መጠን" በዓይነት የተገለፀ መጠንንም ይጨምራል፤
2) "የንግድ ሥራ" ማለት፡-

ሀ/ በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣ የንግድ ፣ የሙያ ወይም ቮኬሽናል ሥራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም፣

ለ/ በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ነው ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ ማንኛውም ሥራ ፣ ወይም

ሐ/ ሕንፃ ማከራየትን ሳይጨምር የኩባንያው ዓላማ ምንም ቢሆን ማንኛውም የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚሠራው ማንኛውም ሥራ::

3) "የንግድ ሥራ ሀብት" ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው፤
4) "የንግድ ሥራ ገቢ" ማለት በማናቸውም ሰው አማካኝነት ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ ፣ የንግድ ፣ የግብርና ፣ የሙያ ወይም የጣልቃ ገብ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ፣ በኢትዮጵያ የንግድ ህግ እንደ ንግድ ሥራ ዕውቅና ከተሰጠው ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ ሲሆን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 21 የተሰጠውን ትርጉም ይጨምራል፡፡
5) "ማግኘት" ማለት፣

ሀ/ ለንግድ ሥራ እና ለኪራይ ገቢ ግብር፤

1) በአክሩዋል በተሰብሳቢና ተከፋይ የሒሣብ አያያዝ ዘዴ ሒሳቡን ለሚይዝ ግብር ከፋይ ፣ ለመቀበል

Proclamation shall have the meaning in the Regional Tax Administration Proclamation unless defined otherwise in this Proclamation. In addition,for the Purpose of this Proclamation:-

1/ "Amount" includes an amount-in-kind;

2/ "Business" means

a. Any industrial,commercial, professional,or vocational activity conducted for profit and whether conducted continuously or short-term, but does not include the rendering of services as an employeeorthe rental of buildings;
b. any other activity recognised as a trade under the Commercial Code; or
c. any activity, other than the rental of buildings, of a share company orprivate limited company whatever the objects of the company;

3/ "Business asset" means an asset held or used in the conduct of a business wholly or partly to derive business imcome

4/ "Business income" means an income found from any industrial, commercial, agricultural, professioal or vocastional activity or any other activity recongnized as business by the commercial code of Ethiopia and carried on by any person for profit, and shall include definition that has been rendered by Article 21 of this proclamation;

5/ "Derive" means:

a/ for the business and rental income tax:

1/ for a tax payer accounting for on an accruals basis, the arising of the right to receive; or

2/ for a tax payer accounting for tax on a

የሚያስችል መብት ማግኘት፣

2) ሒሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ለሚይዝ ግብር ከፋይ ፣ መቀበል ፣ ወይም

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተጣለ ማንኛውም ሌላ ግብር፣ መቀበል ነው፡፡

6. "የትርፍ ድርሻ" ማለት አንድ ድርጅት ለአባላቱ የሚያከፋፍለው የትርፍ ድርሻ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ የድርጅቱ ካፒታል በከፊል ሲቀንስ ለአባሉ በአባልነቱ ተመላሽ የሚደረግለት ከካፒታሉ ውስጥ ከተቀነሰው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፣

ለ/ ድርጅቱ መልሶ በመሸጡ ወይም በመዘጋቱ ወይም ኩባንያው በመፍረሱ ወይም ሽርክና በመቋረጡ ምክንያት የአባልነት ጥቅም ሲሰረዝ ለአባሉ ተመላሽ የተደረገለት በካፒታሉ ውስጥ ከነበረው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፣

ሐ/ ድርጅቱ ለአንድ የድርጅት አባል ወይም ከአባሉ ጋር ግንኙት ላለው ሰው ትርፍ የማከፋፈል ውጤት በሚያስከትል ግብይት ያበደረው ማንኛውም የገንዘብ መጠን ፣ ለአንድ ሀብት ወይም አገልግሎት የፈጸመው ክፍያ ፣የቀረበ ማንኛውም ሀብት ወይም አገልግሎት ዋጋ ፣ ወይም የተተወ የብድር ዕዳ ፣

7) "ተቀጣሪ" ማለት ራሱን ችሎ የሚሠራን የሥራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ሲሆን የድርጅት ዳይሬክተርን ወይም በድርጅቱ አመራርውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የሕዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግሥት ሥራ ኃላፊን ያጠቃልላል፡

8) "ቀጣሪ" ማለት ተቀጣሪን የቀጠረ ወይም ለተቀጣሪው ደመወዝ የሚከፍል ሰው ነው፡፡

cash basis, received; or

b/ For any other tax imposed under this Proclamation, received.

6. "Dividend" means a distribution of profits by a body to a member and includes the following:

a/ an amount returned by a body to amember in respect of a membership interest on a partial reduction in the capital of the body to the extent that the amount returned exceeds the amount by which the nominal value of the membership interest was reduced;

b. an amount returned by a body to a member on redemption or cancellation of a membership interest, including on liquidation of a company or termination of a partnership, to the extent that the amount returned exceeds the nominal value of the membership interest;

c. An amount of loan, payment for an asset or service, value of any asset or services provided, or any debt obligation released, by a body to, or in favour of, a member or a related person of a member to the extent that the transaction is, in substance, a distribution of profits;

7. "Employee" means an individual engaged whether on a permanent or temporary basis, to perform services under the direction and control of another person, other than as an independent contractor, and includes a director or other holder of an office in the management of a body, and government appointees and elected persons holding public offices;
8. "Employer" means a person who engages or remunerates an employee;
9. "Employment income" means any payment or benefit that comes from employment, in cash

9) “ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ” ማለት ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 የተሰጠውን ትርጉም ይጨምራል፡፡

10) “ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ” ማለት በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ “ሠ” ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ ነው፤

11) “የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች” ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ የተደነገጉት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ናቸው፤

12) “ጠቅላላ ገቢ” ማለት ወጪዎች ተቀናሽ ከመደረጋቸው በፊት አንድ ሰው ያገኘው በሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” ሥር የሚወድቅ ጠቅላላ ገቢ ነው፤

13) “የማይንቀሳቀስ ንብረት” በአንቀጽ 36 በተደነገገው መሠረት በማዕድን ወይም በነዳጅ ሀብት ላይ ያለን መብት ወይም የማዕድን ወይም የነዳጅ መረጃን ይጨምራል፤

14) “ገቢ” ማለት መደበኛ ያልሆነ ገቢን ጨምሮ ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ወይም በማንኛውም መንገድ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው፣በስሙ የተያዘለት ወይም የተቀበለው ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ነው፤

15) “ራሱን የቻለ ሥራ ተቋራጭ” ማለት ሥራውን በአመዛኙ በራሱ የመምራትና የመቆጣጠር በቂ ሥልጣን በሚሰጠው ውል መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤

16) “ወለድ” ማለት ገንዘብን ለመጠቀም ወይም የክፍያ ጊዜን ለማራዘም በየጊዜው ወይም በአንድ ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ቅናሽን፣ፕሪሚየምን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ክፍያዎችንም ይጨምራል፤

17) “የሥራ አመራር ክፍያ” ማለት ለሥራ አመራር ወይም አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን አይጨምርም፤

18) “ባለስልጣን” ማለት የቤኒሻንጉል ጉመዝ ክልላዊ መንግሰት ገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡

or in-kind,includes a definition rendered under Article 12 of this proclamation;

10. “Exempt income” means income exempt from tax under schedule “E” of this proclamation;

11. “Financial reporting standards” means the financial reporting standards stipulated under theFinancial Reporting Proclamation;

12. “Gross income” in relation to a person, means the total income taxable under Schedules “B” or “C” derived by the person without deduction of expenditures;

13. “Immovable asset” includes a mining or petroleum right, or mining or petroleum information, as defined in Article 36 of this Proclamation;

14. “Income” meanseveryform of economic benefit, including non-recurring gains, in cash or kind from whatever source derived andin whatever form paid, credited, or received;

15. “Independent contractor” means an individual engaged to perform services under an agreement by which the indibidual retains substantial authority to direct and control the manner in whichthe services are to be performed;

16. “Interest” means a periodic or lump sum amount , however describedas consideration for the use of money or being given time to pay, and includes a discount,premium,or other functionally equivalent amount;

17. “Management fee” means an amount as consideration for the rendering of any managerial or administrative service, but does not include employment income;

18. “Authority” mean the Benishangul Gumuz region Revenues Authority;

19. "Bureau" or “Bureau Head" means the

19) "ቢሮ" ወይም "ቢሮ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የየገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ነው፤

20) "መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ነው፡፡

21.) "መቀበል" የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ ግብር ከፋዩ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በሕግ መሠረት ገንዘቡ በግብር ከፋዩ ስም ጥቅም ላይ ሲውል፣
ለ/ ለግብር ከፋዩ ጥቅም ተብሎ ገንዘቡ መልሶ ሥራ ላይ ሲውል ወይም ሲጠራቀም ወይም ደግሞ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፣
ሐ/ የግብር ከፋዩ ጥቅም ወደ ባንክ ሂሳብ ውስጥ ሲገባ ወይም ወደ መጠባበቂያ ገንዘብ ሲዘዋወር ፣ ወይም
መ/ በሌላ በማናቸውም መልኩ ለግብር ከፋዩ የተያዘለት ሲሆን፣

22) "ሮያሊቲ" ማለት ከዚህ በታች ከተመለከቱት ለማንኛውም ጉዳይ በአንድ ጊዜ ወይም በየጊዜው የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው፡፡

ሀ/ ማንኛውንም የሥነ-ጽሑፍ ፣ የሥነ-ጥበብ፣ ወይም የሳይንሳዊ ሥራ የቅጂ መብት ሲሆን፣ የሲኒማቶግራፊ ፊልሞችና ለሬድዮ ፣ ለቴሌቪዥን ወይም ለኢንተርኔት ሥርጭት የሚውሉ ፊልሞችና ፣ ቴፖችን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘትን ይጨምራል፤
ለ/ ከቴሌቪዥን ወይም ከሬድዮ ወይም ከኢንተርኔት ሥርጭት ጋር ተያይዞ በሳተላይት ፣ በኬብል ፣ በኦፕቲክ ፋይበር ፣ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ወይም የሚታዩ ምስሎችን ፣ ወይም ድምፆችን ወይም ሁለቱንም መቀበል ወይም ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት ፣
ሐ/ ማንኛውንም የፈጠራ ባለቤትነት መብት ፣ ፈጠራ፣ የንግድ ምልክት፣ ንድፍ ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ የሚስጥር ቀመር ወይም ሂደት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሀብት ወይም መብት መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፣
መ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ ፣ የንግድ ወይም ሳይንሳዊ መሣሪያ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘት፤
ሠ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ ፣የንግድ ወይም ሳይንሳዊ ተሞክሮ የሚመለከት መረጃ መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፤
ረ/ በዚህ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ - ሠ) የተዘረዘሩትን ሀብቶች ወይም መብቶች መጠቀም እንዲቻል በተጨማሪነትና በተቀጽላነት የሚሰጥ ድጋፍ፤

23) "የግብር ዓመት" ማለት፣

ሀ/ ለግለሰብ ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቂያ ፈቃድ ካልሰጠ እና በጽሑፍ ማስታወቂያው የተወሰኑትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላት ግለሰቡ

Benishangul Gumuz Regional State the Financeand Economic Development Bureau or the Head of Finance and Economic Bureau;

20. "Regional Administrative council " means the Benishangul Gumuz Regional State council of Administration.

21. "Received" includes:

a) Applied on behalf of the Taxpayer either at the request of the Taxpayer or under any law;

b) Reinvested, accumulated or capitalized for the benefit of the taxpayer;

c) Credited to an account or carried to a reserve for the benefit of the taxpayer; or

d) Otherwise made available to the taxpayer.

22/ "Royalty" means a periodic or lump sum amount as consideration for any of the following:

a. The use of, or the right to use any copyright of literary, artistic, or scientific work, including cinematography films, and films and tapes for radio, television, or internet broadcasting;

b. The receipt of, or right to receive, visual images or sounds, or both, transmitted by satellite, cable, optic fiber, or similar technology in connection with television, radio, or internet broadcasting

c. The use of, or the right to use any patent, invention, trademark, design or model, plan, secret formula or process, or other like asset or right;

d. The use of, or the right to use any

የራሱን የሂሳብ ዓመት ካልተጠቀመ በስተቀር ፣ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው የአንድ ዓመት ጊዜ ነው፤

ለ/ ለድርጅት ሲሆን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት፤ ወይም

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተወሰነው የመሸጋገሪያ የሂሳብ ዓመት ነው፤

24) "ግብር ከፋይ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፤

25) "የቴክኒክ ክፍያ" ማለት ለቴክኒካዊ፣ ሙያዊ ፣ ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ሲሆን ፣ የቴክኒክ ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን ለመጠቀም የሚከፈል ክፍያን ይጨምራል፤

26) "የንግድ ዕቃ" የሚከተሉትንም ይጨምራል፤

ሀ/ ማንኛውም የተመረተ ፣ የተፈበረከ ፣ የተገዛ ወይም ለማምረት ፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ ፣

ለ/ በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ፣ ወይም

ሐ/ ለጭነት ወይም ለሥራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ፤

27) "ዋና ባለቤትነት" ማለት በድርጅት ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ድርጅት ወይም ድርጅቶች ወይም በግለሰቦች አማካኝነት ወይም በግለሰብ ባለቤትነት ሥር ባልሆነ ተቋም አማካኝነት የተያዘ የባለቤትነት ጥቅም ነው፤

28) "ድርጅት" ማለት ኩባንያ ፣ የሽርክና ማህበር፣የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ወይም ሌላ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር የተመሠረተ የሰዎች ድርጅት ነው፡፡

29) "ኩባንያ" ማለት የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ለመሥራት የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣በሌላ ሀገር ሕግ መሠረት የተመሠረተን ተመሳሳይ የንግድ ድርጅት ይጨምራል፡፡

30) "ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው" ማለት ከሚከፍለው ክፍያ ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል አስር

industrial, commercial, or scientific equipment;

e. The use of, or the right to use any information concerning industrial, commercial, or scientific experience;

f. The supply of assistance that is ancillary and subsidiary to, and is furnished as a means of enabling the application or enjoyment of asset or a right referred to in paragraphs (a) - (e) of this sub-article.

23/ "Tax year" means:

a. for an individual, the one-year period from 1st Hamle to 30th Sene, unless the Authority has granted permission,by notice in writing and subject to such conditions as may be specified by the Authority in the notice, for the individual to use its accounting year as the individual's tax year;

b. for a body, the accounting year of the body; or

c. a transitional accounting year as determined under Article 28 of this Proclamation;

24/ "Taxpayer" means a person liable for tax under this Proclamation;

25/ "Technical fee" means a fee for technical, professional, or consultancy services, including a fee for the provision of services of technical or other personnel;

26/ "Trading stock" includes:

a. anything produced, manufactured, purchase or otherwise acquired for manufacture, sale, or exchange;

b. any raw materials or consumables used inaproduction or manufacturing process; or livestock, but not including animals፣

c. used as beasts of burden or working beasts;

መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው፡፡

31) "ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ግብር ተቀንሶ የሚያዝበት ገቢ ማለት ነው፡፡

32) "ንፋስ አመጣሽ ትርፍ" ማለት ማንኛውም ያለልፋት የሚገኝ፣ ያልተጠበቀ ወይም ሌላ ተደጋግሞ የማይገኝ ትርፍ ነው፡፡

33) "ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡት ደንቦች መሠረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሣቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን ነው፣

**አንቀጽ 3. <u>የግብር ከፋይ ደረጃዎች</u>**

1) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ይኖራሉ፡-

ሀ/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፣

1. ድርጅት፣ ወይም
2. ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር 1,000,000 / አንድ ሚሊዮን ብር / ወይም ከዚህ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው ፤

ለ/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር1,000,000 / አንድ ሚሊዮን ብር / የሚያንስ ነገር ግን ብር 500,000 / አምስት መቶ ሺህ ብር / እና ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው ፤

ሐ/ ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500,000 / አምስት መቶ ሺህ ብር / የሚያንስ ሰው ነው፡፡

2) ግብር ከፋዩ የደረጃ ለውጥ ማድረግ የሚያስችል ሽያጭ በግብር ዘመኑ መፈጸሙን ከአረጋገጠ ከሚቀጥለው በጀት አመት ጀምሮ ለደረጃው የተቀመጡ ግዴታዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።

3) የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቀውን ገቢ ወይም የሚያገኘውን ሌላ መረጃመሠረትበማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይወስናል፡፡

4) ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውንና ግብር ከፋዮችን የደረጃ "ሀ" ፣ የደረጃ "ለ" ወይም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ብሎ ለመመደብ የሚያስችለውን ዓመታዊ ጠቅላላ የገቢ መጠን በኢኮኖሚ ጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ማሻሻል አለበት፡፡

**አንቀጽ 4 <u>በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት</u>**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3)፣(4) እና (5) ድንጋጌዎች

27/ "underlying ownership", in relation to a body, means a membership interest in the body held directly, or indirectly through an interposed body or bodies, by an individual or by an entity not ultimately owned by individuals;

28/ "Body" means a company, a partnership,a public development enterprise or a public financial agency or other formulated public body in Ethiopia or foreign country;

29/ "Company" means a commercial business organisation established in accordance with the Commercial Code of Ethiopia and having legal personality, and includes any equivalent entity incorporated or formed under a foreign law;

30/ Withholding agent" means a person liable to withhold tax under Part Ten of this proclamation from a payment made by the person and includes a person required to self-withold tax under article 93 of this proclamation from an amount received by the person; and

31/ "Withholding income" mean income from which tax is required to be withheld under Part Ten of this Proclamation.

32/ "Windfall gain" mean any unearned, Unexpected or other non-recurring gain.

33/ 'Taxable Income'' shall mean the amount of income subject to tax after deduction of all expenses and other deductible items allowed under this proclamation and regulations issued there under.

**Article 3. <u>Categories of Taxpayer</u>**

እንደተጠበቁ ሆነው፣ "በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት" የሚባለው ማናቸውም ሰው የንግድ ሥራውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያከናውንበት ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ነው፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

ሀ/ ዋነኛ ተግባሩ የድርጅቱ አገናኝ ሆኖ ከሚያገለግለው ጽሕፈት ቤት በስተቀር የአስተዳደር ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፣ ቢሮ፣ ፋብሪካ፣ መጋዘን ወይም ወርክሾፕ፤

ለ/ የማዕድን ማምረቻ ሥፍራ፣ የነዳጅ ወይም የጋዝ ጉድጓድ፣ የግንባታ ጠጠር ማምረቻ፣ ወይም ሌላ ማናቸውም የተፈጥሮ ሀብት ፍለጋ፣ ወይም ማምረት ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፤

ሐ/ ለአንድ ወይም ለተያያዙ ፕሮጀክቶች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ183 (አንድ መቶ ሰማንያ ሦስት) ቀናት በላይ ለሆነ ጊዜ ተቀጣሪዎችን ወይም ሌሎች ሠራተኞችን በመመደብ የምክር አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች ማናቸውም አገልግሎቶች የሚሰጡበት ቦታ፤

3. የግንባታው ሥራ፣ ፕሮጀክቱ ወይም የሥራ እንቅስቀሴው ከ183 (አንድ መቶ ሰማንያ ሦስት) ቀናት በላይ የሚቆይ እስከሆነ ድረስ የህንፃ ግንባታ ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ፣ የግንባታ፣ የመገጣጠም ወይም የተከላ ፕሮጀክት ወይም ከእነዚህ ጋር የተገናኙ የቁጥጥር ሥራዎች በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል በመደበኛ የንግድ ሥራ አካሄድ ከሚያከናውነው ተግባር በስተቀር ማናቸውም ሰው "ወካይ" ተብሎ ለሚጠራ ሌላ ሰው ወኪል በመሆን በሌላ ሰው ስም የሚሰራ በሚሆንበት ጊዜ ወኪሉ የወካዩ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ነው የሚባለው ፡-

ሀ/ በወካዩ ስም በቋሚነት ውሎችን የሚደራደር፤ ወይም

ለ/ በወካዩ ስም የንግድ ዕቃዎችን ለማስረከብ አክማችቶ የሚይዝ ከሆነ ነው፡፡

5. በዚህ አንቀጽ "ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል" ማለት በሚወክለው ሰው ቁጥጥር ስር ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚሠራ ደላላ ፣ የኮሚሽን ወኪል ወይም ሌላ ወኪል ሲሆን ፣ የንግድ

1/ For the purposes of this Proclamation there shall be the following categories of Business taxpayers.

a. category "A" taxpayer being

1/ a company, or

2/ any other person having an annual gross income of Birr 1,000,000 or more;

b. category "B" taxpayer being a person, other than a Company, having an annual gross income of Birr 500,000 or more but less than 1,000,000

c. category "C" taxpayer being a person other than a Company, having an annual gross income of less than Birr 500,000

2/ The taxpayer shall implement duties set for the standard commencing from the new budget year, where it assures in the budget year that enables selling amount for change of standard;

3/ The Authority may, on the basis of income declarations filed by a taxpayer or any other information available to the Authority, determine whether the taxpayer's category has changed for a tax year.

4/ The Bureau shall, after ascertaining by economic analysis, change the annual gross income thresholds in sub-Article 1 of this Article for the classification of a taxpayer as a category "A" taxpayer category "B" Taxpayer or category "C" taxpayer.

**Article 4. Permanent Establishment**

1. Subject to the provisions of sub-articles (2),

ወይም የፋይናንስ ግንኙነታቸው ራሳቸውን ችለው ከሚሠሩ ሰዎች የተለየ የሆነውን በብቸኝነት ወይም በዋነኛነት ለአንድ ሰው ወኪል በመሆን የሚሠሩትን አይጨምርም፡፡

**አንቀጽ 5. ነዋሪነት**

1. የሚከተሉት የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ናቸው፡-

ሀ/ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ፤

ለ/ ነዋሪ የሆነ ድርጅት፤

ሐ/ የክልሉ መንግስት እንዲሁም ማናቸውም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዞን አስተዳደር ; ወረዳ አስተዳደር ወይም የከተማ አስተዳደር፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው፤ አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለው፤

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ183 (አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት) ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ ፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት "የተያዘው የግብር ዓመት" ተብሎ ለሚጠቀሰው ለአንድ የግብር ዓመት ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ባለፈው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ በተያዘው የግብር ዓመት እንደነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ቀን አንስቶ ነው፡፡

4. አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተያዘው የግብር ዓመት ነዋሪ ሆኖ፤ ነገር ግን በሚቀጥለው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ፤ በተያዘው የግብር ዓመት እንደ ነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ግለሰቡ ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኖረበት ቀን በፊት ላለው ጊዜ ነው፡፡

5. አንድ ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ወይም የተመሠረተ እንደሆነ፤

ለ/ ወሳኝ የሆነ አመራር የሚያካሂድበት ሥፍራ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እንደሆነ ነው፡፡

6. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ነው፡፡

7. ነዋሪ ያልሆነ ሰው የሚባለው ማንኛውም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

**አንቀጽ 6. የገቢ ምንጭ**

1. አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ክፍያው የሚፈጸምበት ሥፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ

(3), (4) and (5) of this Article, "a permanent establishment" is a fixed place of business through which the business of a person is wholly or partly conducted.

2. The following are specifically treated as a permanent establishment:

a) A place of management, office, factory, ware house, of workshop, but does not include an office that has representation of the person's business as its sole activity;

b) A mine site, oil or gas well, quarry, or other place of exploration for, or extraction of, natural resources;

c) The Funishing of services, including consultancy services, by a person, including through employees or other personnel engaged by the person for such purpose, but only when activities of that nature continue for the same or a connected project for a period or periods aggregating more than 183 (one hundred eighty three) days in any one-year period.

3. A building site, or a construction, assembly, or installation project, or Supervisory activities connected with such site or project shall be a permanent establishment only when the site, project, or activities continue for more than ninety days.

4/ Despite sub-articles (1) and (2) of this Article, when a person, other than an agent of independent status acting in the ordinary course of business, acts on behalf of another person (referred to as the "principal"), the first-mentioned person shall be a permanent establishment of the principal if the person:

a. regularly negotiates contracts on behalf of the principal ; or

b. Maintains a stock of goods from which the

ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ፣ ወይም

ለ/ የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ክፍያው ለተቀጣሪው ከተፈፀመ ፣ ነው፡፡

2. በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ አማካኝነት ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያገኘውን ገቢ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያፈራው የንግድ ሥራ ገቢ ከኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ገቢ ይሆናል፡፡

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የንግድ ሥራ ገቢ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅቱ አማካይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ ሲሆን፣

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካይነት ከሚሸጣቸው እቃዎች ወይም ሸቀጦች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ እቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ኢትዮጵያ ውስጥ በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ፣

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት የሚሰራድርጅት ከሚያከናውናቸው ማናቸውም የንግድ ሥራዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ በማከናወን የሚያገኘው ገቢ፣

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) እና (3) የተመለከተው ቢኖርም፣ የሚከተሉት ገቢዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የመነጩ ገቢዎች ናቸው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ለአንድ ሰው የሚከፍለው የትርፍ ድርሻ፣

ለ/ የሚከተሉትን ሀብቶች በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብት ወይም

person regularly delivers goods on behalf of the principal.

5/ In this Article, "agent of independent status" means a broker, general commission agent, or other agent acting independently of the person that they represent, but does not include a person who acts solely or principally for another person if their commercial and financial relations differ from those that would have been made between independent person.

**Article 5. <u>Residence</u>**

1/ The following are residents of Ethiopia:

a) a resident individual;

b) a resident body;

c) The regional government, as well as, any zone administration , woreda or city administration of the region.

2/ Subject to sub-Articles (3) and (4) of this Article, a resident individual is an individual who:

a) has a domicile in Ethiopia;

b) is present in Ethiopia, contineously or intermittently, for more than 183 days in a one-year period.

3/ An individual who is a resident individual under sub-article (2) of this Article for a tax year (referred to as the "current tax year"), but who was not a resident individual for the preceding tax year shall be treated as a resident individual in the current tax year

2. በአንቀጽ 55 መሠረት ግብር የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሚንቀሳቀስ ሀብት፣

ሐ/ የሚከተሉትን ሀብቶች በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ፡-

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብት፣
2. ከ50% በላይ በሚሆነው በሀብቱ ዋጋ ላይ ያለው ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተዛመዱ ድርጅቶች የተያዘ በሚሆንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የማይንቀሳቀስ ሀብቱ ላይ ያለ ጥቅም፣

3/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ያወጣው አክሲዮን ወይም ቦንድ፣

መ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መድን ለተገባለት አደጋ (ስጋት) የሚከፈል የመድን አረቦን፣

ሠ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የመዝናኛ ወይም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፣

ረ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የዕድል ሙከራዎችን በማሸነፍ የሚገኝ ገቢ፣

ሰ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ወለድ ፣ ሮያሊቲ ፣ የሥራ አመራር ክፍያ ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት፡-

1/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካይነት ውጭ ሀገር ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ ያወጣውን ወጪ ሳይጨምር ፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው የሚፈጽመው ክፍያ፣

2/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ወስጥ ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ የሚፈጽመው ክፍያ፣

5. ከኢትዮጵያ ውስጥ ያልመነጨ ማንኛውም ገቢ የውጭ ሀገር ገቢ ነው፡፡

**አንቀጽ 7.** **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

1/ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው በግል የሚያርሱ ገበሬዎችን ሳይጨምር በፌደራሉ ሕገ መንግሰት አንቀጽ 97 እና 98 ለክልል መንግስታት ተለይቶ በተሰጠው የግብር ስልጣን ለሚሸፈኑ ግብር ከፋዮች ላይ ነው።

2) አዋጁ በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በክልሉ ውስጥ እና

only for the period commencing on the day on which the individual was first present in Ethiopia.

4/ An individual who is a resident individual under sub-article (2) of this Article for the current tax year but who is not a resident individual for the following tax year shall be treated as a resident individual in the current tax year only for the period ending on the last day on which the individual was present in Ethiopia.

5/ A resident body is a body that:

a. is incorporated or formed in Ethiopia; or

b. has its place of effective Management in Ethiopia.

6/ A resident company is company that is a Resident body.

7/ A non-resident is any person who is not a resident of Ethiopia.

**Article 6. <u>Source of Income</u>**

1. Employement income derived by an employee shall be ethiopian source income;

   a. To the extent that it is derived in respect of employment exercised in Ethiopia, wherever paid; or

   b. If it is paid to the employee by, or on behalf of, the government of Ethiopia, wherever the employment is exercised.

2. Business income derived by a resident of Ethiopia shall be Ethiopian source income except to the extent that it is attributable to a business conducted by the resident through a permanent establishement outside Ethiopia;

ከክልሉ ውጭ በሚያገኙት በማናቸውም ገቢ ላይተፈጻሚ ይሆናል።

3/ በክልሉ ውስጥ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በተመለከተ አዋጁ ተፈጻሚነት የሚኖረው በክልሉ ውስጥ በሚያገኙት ገቢ ላይ ነው።

**አንቀጽ 8. የገቢ ሠንጠረዦች**

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው የገቢ ግብር በሚከተሉት ሠንጠረዦች መሠረት ይከፈላል፡፡
   ሀ/ ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣
   ለ/ ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፣
   ሐ/ ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ
   መ/ ሠንጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች፣
   ሠ/ ሠንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች፣
2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 61(2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ገቢ ያገኝ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው በዚያው ሠንጠረዥ ሥር የዓመቱን ግብር ይከፍላል፡፡

**አንቀጽ 9. የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ**

ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሠንጠረዥ “ሀ” ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ

**አንቀጽ 10. ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል**

1) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 81 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚያገኘው ጠቅላላ የወር ወይም የወሩ ክፊል ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 በተወሰኑት ወሳኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ ወር ግብር ይከፍላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከመቀጠር በሚገኝ ወርሀዊ ገቢ ላይ የሚጣለው የገቢ ግብር ተቀጣሪው በአንድ ወር ውስጥ በተቀበለው ጠቅላላ ወርሃዊ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት ተፈፃሚ የሚሆነውን መጣኔ መሠረት በማድረግ ይሰላል፡፡
3) ተቀጣሪው በመቀጠር የሚገኘውን ገቢ ለማግኘት የሚያወጣው ማንኛውም ወጪ በተቀናሽ ሊያዝለት አይችልም፡፡
4) ለዚህ ሠንጠረዥና ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 አፈፃፀም ሲባል፣ በነሐሴና በጳጉሜ ወራት የሚከፈለው የቅጥር ገቢ ተደምሮ

3. Business income derived by a non-resident shall be Ethiopian source income to the extent that it attributable to:

a. business conducted by the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia;

b. sales in Ethiopia by the non-resident of goods or merchandise of the same or similar kind as those sold by the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia; or

c. Anyother business activity conducted by the non-resident in Ethiopia of the same or similar kind as that conductedby the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia.

4/ Despite sub-articles (1), (2), and (3) of this Article, income derived by a person shall be Ethiopian source income if it is:

a. a dividend paid to the person by a resident body;

b. rental income from the lease of

1/ immovable property located in Ethiopia;

2/ movable property located in Ethiopia subject to tax under Article 55 of his Proclamation;

c/ a gain arising from the disposal of the following:

1. immovable property located in Ethiopia;

2. a membership interest in a body, if more than 50% of the value of the interest is derived, directly or indirectly through one or more interposed bodies, from immovable property located in Ethiopia;

3/ shares in, or bonds issued by, a residen company;

d/ an insurance premium relating to the insurance of a risk in Ethiopia;

እንደ የአንድ ወር ደመወዝ ግብር ይከፈልበታል፡፡

5) በአንድ ተቀጣሪ ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 80 (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ የተደረገ እንደሆነ በመቀጠር በተገኘው ገቢ ላይ ተቀጣሪው የከፈለው ታክስ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ቀጣሪው በአንቀጽ 84 መሠረት ከተቀጣሪው የሚፈለገውን የገቢ ግብር ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ ግብሩ እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 11.** **<u>በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ መጣኔዎች</u>** :-

ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ለሚጣለው ግብር ተፈፃሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በብር | ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይተፈፃሚ የሚሆን መጣኔ |
|---|---|
| 0 -- 600 | 0% |
| 601---1650 | 10% |
| 1,651--3,200 | 15% |
| 3,201--5,250 | 20% |
| 5,251--7,800 | 25% |
| 7,801--10,900 | 30% |
| ከ10,900 በላይ | 35% |

**አንቀጽ 12 .** **<u>ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ</u>**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ ከመቀጠር የሚገኙ ገቢዎች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ ሠራተኛው ካለፈው፣ አሁን ካለው ወይም ወደፊት ከሚመጣው ቅጥር ጋር በተያያዘ የተቀበለው ደመወዝ፣ ምንዳ፣ አበል፣ ጉርሻ፣ ኮሚሽን፣ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማበረታቻ ስጦታ ወይም ሌላ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ፤

ለ/ ያለፈን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊትን ቅጥር አስመልክቶ ሠራተኛው የሚቀበለው የዓይነት ጥቅማ ጥቅም ዋጋ፤

e/ income from a performance or sporting event taking place in Ethiopia;

f/ winnings from a game of chance held in Ethiopia;

g/ interest, a royalty, management fee, technical fee, or other income subject to tax under this Proclamation:

1/ paid to the person by a resident of Ethiopia, other than as an expenditure of a business conducted by theresident through a permanent establishment outside Ethiopia;

2/ paid to the person by a non-resident as an expenditure of a business conducted by the non-resident Through a permanent establishment in Ethiopia.

5/ Foreign income is any income that is not Ethiopian source income.

**Article 7.** <u>**Scope of Application**</u>

1/ This proclamation shall apply to the national Region power of taxation of the region as prescribed by articles 97 and 98 of the federal constitution with the excluding of private farmers;

2/ The proclamation shall apply to the residents of the region on any income that shall be generated in and outside of the region;

3/ The proclamation shall be applicable on income generated in the region, with regard to non-residents of the region.

**Article 8.** <u>**Schedules of Income**</u>

1. The proclamation provides for the taxation of income in accordance with the following schedules;

   a. Schedule 'A; income from employment;

   b. schedule 'B; income from rental of buildings;

   c. schedule 'C; income from business;

ሐ/ ተቀጣሪው ከሥራ ሲቀነስ፣ ሥራውን ሲለቅ ወይም ሥራውን እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብን ጨምሮ የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በፈቃደኝነት፣ በስምምነት ወይም በዳኝነት ውሳኔ መሠረት የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን ፤

2. በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም፡፡

3. ማንኛውም ቀጣሪ ተቀጣሪው መክፈል የሚኖርበትን ግብር ከተቀጣሪው ገቢ ላይ ሳይቀንስ ራሱ ለተቀጣሪው በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለለት እንደሆነ፣ በቀጣሪው የተከፈለው የግብር መጠን ተቀጣሪው ከመቀጠር ከሚያገኘው ግብር በሚከፈልበት የገንዘብ መጠን ላይ ተደምሮ ግብሩ ይሰላል፡፡

4. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ከደመወዝ ሌላ በዓይነት የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች ዋጋ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አልፎ አልፎ የሚገኝ ተጠቃለው የሚከፈል ገቢዎች የሚወሰንበትንና ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ደንብ ያወጣል፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ</u>**

**አንቀጽ 13. <u>በቤት ኪራይ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል</u>**

1) ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 በተመለከተው መጣኔ ወይም ምጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

2) በግብር ዓመቱ አንድ ግብር ከፋይ ከቤት ኪራይ በሚያገኘው ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ሥር የተመለከቱትን መጣኔዎች ግብር በሚከፈልበት ዓመታዊ ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

3) ይህ ሠንጠረዥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 መሠረት የኪራይ ገቢ ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 1<u>4 . የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔዎች</u>**

1. በድርጅቶች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የግብር ምጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ) ነው፡፡
2. በግለሰቦች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

d. schedule 'D; other income;

e. schedule 'E; exempt income;

2/ Subject to Article 61(2) of this Proclamation, a taxpayer that derives income from different sources subject to tax under the same Schedule for a tax year shall be taxable under the Schedule on the total income for the year.

**Article 9. <u>Obligation to Pay Income Tax</u>**

Every person deriving income shall pay income tax in accordance with this Proclamation and the Tax Administration Proclamation.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>SCHEDULE 'A' - INCOME FROM</u>**

**<u>EMPLOYMENT</u>**

**Article 10. <u>Imposition of Employment</u>**

**<u>Income Tax</u>**

1/ Without prejudice to Article 81 of this Proclamation, Employment income tax shall be Imposed for each calendar month at the rate or rates specified in Article 11 of this Proclamation on an employee who receives employment income during the month.

2/ The employment income tax imposed on an employee under sub-article (1) of this Article for a month shall be calculated by applying the rate or rates of tax applicable to the employee under Article 11 of this Proclamation to the total employment income received by the employee for the month.

3/ An employee shall not be allowed a deduction for any expenditure incurred in deriving employment income.

4/ For the purposes of this Schedule and Article 84 of this Proclamation, the employment income attributable to the months of Nehassie and Pagumen shall be aggregated and treated as the employment

| ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት | የኪራይ ገቢ ግብር □ምጣኔ |
|---|---|
| 0 -- 7,200 | 0% |
| 7,201 -- 19,800 | 10% |
| 19,801 -- 38,4□0 | 15% |
| 38,401 -- 63,□00 | 20% |
| 63,001 -- 93,600 | 25% |
| 93,601 -- 130,800 | 30% |
| ከ130,800 በላይ | 35% |

**አንቀጽ 15 . ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ**

1. የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ የኪራይ ገቢ ነው የሚባለው ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ቤት በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

 ሀ/ የኪራይ ዋጋ ጭማሪን ወይም ተመሳሳይ ክፍያዎችን ጨምሮ፣ በኪራይ ውሉ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ የሚያገኘው ማናቸውም የገንዘብ መጠን፤

 ለ/ በኪራይ ውሉ መሠረት ተከራዩ አከራዩን በመወከል በግብር ዓመቱ ለሌሎች የሚከፍላቸው ክፍያዎች፤

 ሐ/ ግብር ከፋዩ ጉዳቱን ለማስተካከል ያልተጠቀመበት እና በቤቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማስተካከያ ይሆን ዘንድ የያዘው እና በግብር ዓመቱ ለግብር ከፋዩ ገቢ የተደረገው ማንኛውም ቦንድ፣ ዋስትና ወይም ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን፤

 መ/ ለግብር ከፋዩ ከሚከፈለው ኪራይ በተጨማሪ በኪራዩ ውል መሠረት ተከራዩ ራሱ ለቤቱ እድሳት ወይም ማሻሻያ የሚያወጣው ገንዘብ

income of a single calendar month.

5/ If Article 80(1) applies to an employee, the employment income tax payable by the employee shall be a final tax on the employment income of the employee and the tax shall be Discharged if the employer has withheld tax from the income in accordance with Article 84 of this Proclamation.

**Article 11. Employment Income Tax Rates**

The rates of employment income tax are :-

| Employment Income (Per month Birr) | Employment Income Tax Rate |
|---|---|
| 0 -- 600 | 0% |
| 601 --1,650 | 10% |
| 1,651 -- 3,200 | 15% |
| 3,201 -- 5,250 | 20% |
| 5,251 -- 7,800 | 25% |
| 7,801 -- 10,900 | 30% |
| Over 10,900 | 35% |

**12. Employment Income**

1/ Subject to sub-articles (2) and (3) of this article, employment income means the following;

a. salary, wages, an allowance, bonus, commission, gratuity, or other remuneration receibed by an employee in respect of a past,

መጠን፤

3. ግብር ከፋዩ ቤቱን ያከራየው ከዕቃዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ፣ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከዕቃዎቹ የተገኘውን የኪራይ ገቢም ያጠቃልላል፡፡
4. ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ የሆነን ገቢ አይጨምርም፡፡
5. በአንድ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ ይያዛሉ፡-
   ሀ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር በግብር ዓመቱ ውስጥ የከፈላቸው ክፍያዎች፤
   ለ/ ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ ማደሻ፣መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ የሚሆን ከቤት፣ ከቤት ዕቃ እና ከመሳሪያ ኪራይ ከሚገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ ሃምሳ በመቶ፤
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ በማናቸውም ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ላለባቸው ግብር ከፋዮች ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡
7. የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ ገቢውን ለማግኘት የወጣና በግብር ከፋዩ የተከፈለ አስፈላጊ የሆነ ወጪ ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ወጪ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-
   ሀ/ ቤቱ ያረፈበት መሬት ኪራይ፤
   ለ/ የጥገና ወጪ፤
   ሐ/ የቤቱ፣ የቤት ዕቃዎችና የመሣሪያዎች የእርጅና ቅናሽ፤
   መ/ ወለድና የመድን አረቦን፤
   ሠ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች፤

**አንቀጽ 16 . <u>የተከራይ አከራዮች</u>**

current, or future employment;

b. The value of fringe benefits received by an employee in respect of a past, current, or future employment;

c. an amount received by an employee on termination of employment, whether paid voluntarily, under an agreement, or as a result of legal proceedings, including any compensation for redundancy or loss of employment, or a golden handshake payment.

2/ Employment income shall not include exempt income;

3/ If an employer pays the employment income tax payable by an employee, in whole or part, without withholding tax from the employment income of the employee, the amount of tax paid by the employer shall be included in the employment income of the employee;

4/ The council of the regional administration shall make regulations for determining the value and taxation, which are payable incomes inclusibely sometimes pursuant to subarticl 1 of this article, of fringe benefits.

## <u>PART THREE</u>

## <u>SCHEDULE 'B' - INCOME</u>

## <u>FROM RENTAL OF BUILDINGS</u>

**Article 13. <u>Imposition of Rental Income Tax</u>**

1/ Rental income tax shall be imposed for each tax year at the rate or rates specified inArticle 14 of this Proclamation on a person renting out a building or buildings who hasTaxable rental income for the year.

2/ Subject to sub-article (3) of this Article, the rental income tax payable by a taxpayer for a tax year shall be calculated by applying the

1) የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው የሚባለው የተከራይ አከራዩ በግብር ዓመቱ ከተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ላይ ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ መጠን ነው፡፡

2) ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 17.** <u>**የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ**</u>

1. ለኪራይ የሚሰራ ቤት ተሰርቶ እንዳለቀ ወይም ቤቱ እንደተከራየ ፣ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የቤቱ ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም የተከራየ መሆኑን ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው ስም፣ አድራሻና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ቤቱ ለሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር ወይም የአካባቢ አስተዳደር ማስታወቅ አለባቸው፡፡
2. የቀበሌው አስተዳደር እና የአካባቢው አስተዳደር በማስታወቂያው መሠረት የተገኘውን መረጃ ለባለሥልጣኑ መግለጽ አለባቸው፡፡

<u>**ክፍል አራት**</u><br>
<u>**ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ**</u><br>
<u>**ምዕራፍ አንድ**</u><br>
<u>**ከንግድ ሥራዎች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል**</u>

**አንቀጽ 18 .** <u>**በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል**</u>

1. በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው ሰው በእያንዳንዱ የግብር ዓመት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች መሠረት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡
2. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት የሚከፍለው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰላው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 የተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች በግብር ከፋዩ የግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ 19 .** <u>**በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ መጣኔዎች**</u>

1. በድርጅት ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ የግብር ምጣኔ ሰላሳ በመቶ (30%) ነው፡፡

rate or rates of tax applicable to the taxpayer under Article 14 of this Proclamation to the taxable rental income of the taxpayer for the year.

3/ This Schedule shall not apply to rental Income subject to tax under Article 55.

**Article 14.** <u>Rental Income Tax Rates</u>

1/ The rate of rental income tax applicable to a body is 30%.

2/ The rates of rental income tax applicable to an individual are:

| Taxable Rental Income (peryear) Birr | Rental Income Tax Rate |
|---|---|
| 0--7,200 | 0% |
| 7,201-- 19,800 | 10% |
| 19,801-- 38,4[illegible]0 | 15% |
| 38,401-- 63,[illegible]00 | 20% |
| 63,001-- 93,600 | 25% |
| 93,601-- 130,800 | 30% |
| Over 130,800 | 35% |

**Article 15.** <u>**Taxable Rental Income**</u>

1/ The taxable rental income of a taxpayer for a tax year is the gross amount of income derived by the taxpayer from the rental of a building or buildings for the year reduced by the total amount of deductions allowed to the taxpayer for the year.

2/ Subject to sub-articles (3) and (4) of this Article, the gross amount of income derived by a taxpayer from the rental of a building for a tax year shall include the following:

2. በግለሰብ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ከንግድ ሥራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በዓመት | የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ |
|---|---|
| 0 -- 7,200 | 0% |
| 7,201 -- 19,800 | 10% |
| 19,801 -- 38,400 | 15% |
| 38,401 -- 63[illegible]0 | 20% |
| 63,001 -- 93,600 | 25% |
| 93,601 -- 130,800 | 30% |
| ከ130,800 በላይ | 35% |

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ግብር የሚከፍሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር በተመለከቱት ምጣኔዎች መሠረት ይሆናል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች" የሚለው" የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 69/2005 ዓ.ም" የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

**አንቀጽ** 20 **. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ**

1. የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የንግድ ሥራ ገቢ ነው የሚባለው ከንግድ ሥራ ከተገኘ ጠቅላላ የግብር ዓመቱ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀዱት ወጪዎች ተቀናሽ ከተደረጉ በኋላ የሚገኘው የገቢ መጠን ነው፡፡
2. በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ፣ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች እና ቢሮ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የአንድ ግብር ከፋይግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ የሚወሰነው ግብር ከፋዩ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት በሚያዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም የገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 21 **. የንግድ ሥራ ገቢ**

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በአንድ የግብር ዓመት የአንድ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር

a. all amounts derived by the taxpayer during the year under the lease agreement, including any lease premium or similar amount;

b. all payments made by the lessee during the year on behalf of the lessor according to the lease agreement;

c. the amount of any bond, security, or similar amount that, during the year, the taxpayer is entitled to retain as a result of damage to the building and that has not been used by the taxpayer in repairing the damage to the building;

d. the value of any renovation or improvement made under the lease agreement to the building when The cost was borne by the lessee in addition to the rent payable to the taxpayer.

3/ If a taxpayer leases a furnished building, the gross amount of income derived by the taxpayer from the lease of the building shall include any amount Attributable to the Lease of the furniture or Equipment.

4/ The gross amount of income Derived by a taxpayer from the lease of a building shall not include exempt Income.

5/ In computing the taxable rental income for a tax year of a taxpayer who does not maintain books of account, a deduction shall be allowed for the following amounts:

a) any fees and charges, but not tax,levied by a State or city administration in respect of the land or building leased and paid by the taxpayer during the year;

b) An amount equal to fifty precent (50%) of

ከፋይ የንግድ ሥራ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ ዕቃዎችን በማስተላለፍ እንዲሁም አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ሥራ ያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ መጠን፤

ለ/ ለንግድ የሚውል ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ የገንዘብ መጠን፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ገቢ ተደርጎ የሚወሰድ ሌላ ማንኛውም የገንዘብ መጠን፤

2. ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ከንግድ ሥራ ሀብቱ የመዝገብ ዋጋ በላይ የሆነው የንግድ ሥራ ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ከተላለፈው ሀብት የተገኘው ገቢ ነው፡፡

4. አንድ የንግድ ሥራ ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተውን የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኘውን ገቢ ለንግድ ሥራው ሀብት የተደረገው ወጪ ከንግድ ሥራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ሲሆን፤

ለ/ ከወጪው በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ አንቀጽ 56 መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

**አንቀጽ 22 . ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች**

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን በተቀናሽ የሚያዙት ወጪዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

ሀ/ በንግድ ሥራው ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፤

ለ/ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በተመለከተው መሠረት የተሠላ በግብር ዓመቱ በግብር ከፋዩ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ የወጣ ወጪ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 በሚወሰነው መሠረት የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ሥራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች

the gross rental income Derived by the taxpayer for the year as an allowance for the repair, maintenance, and depreciation of the building, Furniture and equipment.

6/ The provisions of sub-article 5 of this Article shall not be applicable for taxpayers who are required to maintain books of account under this Proclamation, for any reason what So ever.

7/ In computing the taxable rental income for a tax year of a taxpayer who maintains books of account, a deduction shall be allowed for any expenditures incurred by the taxpayer in deriving rental income and paid during the year including:

a) the cost of the lease of land on which the building is situated;

b) repairs and maintenance;

c) depreciation of the building, furniture and equipment;

d) interest and insurance premiums; and

e) Fees and charges, but not tax, levied

By a State or city administration in Respect of the land or building leased.

**Article 16. Sub-leases**

1/ The taxable rental income of a sub-lessor of a building for a tax year shall be the difference between the total rental income received by the sub-lessor during the year and the total rental income paid to the lessor of the building plus other expenses to the extent necessarily incurred by the sub lessor to generate the income.

2/ The owner of a building who allows a lessee to sub-lease the building shall be liable for the rental income tax payable by the lessee if the lessee fails to pay the tax.

**Article 17. New Rental Building Notification**

እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣

መ/ ግብር ከፋዩ የንግድ ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ሀብትን ሲያስተላልፍ የሚገጥመው ኪሳራ፣

ሠ/ ለግብር ዓመቱ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት የሚፈቀድ ሌላ ማናቸውም ወጪ፣

2/ ግብር የሚከፈልበት ሀብት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ካልሆነ በስተቀር፣ ግብር የሚከፈልበት ሀብት በሚተላለፍበት ጊዜ ለሚደርስ ኪሳራ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) ግን ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) አፈፃፀም፣ የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚደርስ ኪሳራ የሚባለው ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ በሚበልጠው የገንዘብ ልክ ነው፡፡

**አንቀጽ 23 . <u>የወለድ ወጪ</u>**

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግብር ከፋዩ የወሰደውን ብድር ወይም ሌላ ዕዳ ወይም ያደረገውን ስምምነት የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ተግባር ያዋለው እስከሆነ ድረስ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከፈለው ወለድ የግብር ከፋዩ የግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ እንደወጪ ይያዝለታል፡፡

2/ ለሚከተሉት ወጪዎች ተቀናሽ አይፈቀድም፡-

ሀ/ ወለዱ በብሔራዊ ባንክ እና በንግድ ባንኮች መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ ምጣኔ 2% (ሁለት በመቶ) የሚበልጥ ከሆነ በተቀናሽ አይያዝም፣ ነገር ግን ወለዱ፣

1/ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ለተሰጠው የፋይናንስ ተቋም ፣ ወይም

2/ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሰዎች ብድር እንዲሰጥ ለተፈቀደለት የውጭ ሀገር ባንክ፣ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ከሆነ በተቀናሽ ይያዛል፡፡

ለ/ የወለዱ ገቢ ግንኙነት ባለው ሰው የሰንጠረዥ “መ” ሥራ ገቢ ውስጥ ካልተካተተ በስተቀር፣ አንድ ግብር ከፋይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ግንኙነት ላለው ሰው የከፈለው ወይም የሚከፍለው ወለድ ፣

**አንቀጽ 24 . <u>ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች</u>**

1. የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ያደረገው

1/ At the earlier of the time construction Of a rental building is completed or When the building is rented, the owner Of the building and the builder shall Notify the kabele administration and local administration in which the building is located about the completion and the name, address, and TIN of The person Or persons liable for rental income tax With respect to the building.

2/ The kabele administration or Local administration communicate the information contained in the notification to the Authority.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>SCHEDULE ‘C’ — INCOME FROM BUSINESS</u>

## CHAPTER ONE

## <u>IMPOSITION OF BUSINESS INCOME TAX</u>

Article 18. <u>Imposition of Business Income Tax</u>

1/ Subject to the provisions of this Part, business income tax shall be imposed for each tax year at the rate or rates specified in Article 19 of this Proclamation on a person conducting business That has taxable income for the year.

2/ The business income tax payable by a taxpayer for a tax year shall be calculated by applying the rate or rates of tax applicable to the taxpayer under Article 19 of this Proclamation to the taxable income of the taxpayer for The year.

**Article 19. <u>Business Income Tax</u>**<u>Rates</u>

1/ The rate of business income tax Applicable to a body is [30%].

2/ The rates of business income tax applicable to an individual are:

| Taxable | Business |
|---|---|

ስጦታ ተቀናሽ የሚደረገው ስጦታው ለሚከተሉት የተደረገ ሲሆን ነው፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ለተመለከተው የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማኅበር፣ ወይም

ለ/ መንግሥት ባደረገው ጥሪ መሠረት ለልማት፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር፣ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም ወረርሽኝ ለመከላከል ወይም ለተመሳሳይ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት የተደረገ ከሆነ፣ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለግብር ከፋዩ የሚፈቀደው ጠቅላላ ተቀናሽ ከግብር ከፋዩ ግብር ከሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ 10% (አሥር በመቶ) መብለጥ የለበትም፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማኅበር" በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 25 .** **<u>የእርጅና ቅናሽ</u>**

1) የግብር ከፋዩን በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው እና ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ለማድረግ ይፈቀድለታል፡፡

2) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች በየግብር ዓመቱ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

3) አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶችን ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸውን ሀብቶች ያልተጠቀመ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሆኖ፣ የንግድ ሀብቱ ጥቅም

| Income (per year) Birr | Income Tax Rate |
|---|---|
| 0 -- 7,200 | 0% |
| 7,201 -- 19,800 | 10% |
| 19,801 -- 38,400 | 15% |
| 38,401 -- 63,000 | 20% |
| 63,001 -- 93,600 | 25% |
| 93,601 -- 130,800 | 30% |
| Over 130,800 | 35% |

3/ Not with standing sub- article /1/ of this article, micro enterprises shall pay income tax in accordance with rates pursuant to sub-article /2/ of this article

4/ For the purpose of this Article "Micro Enterprises" shall maintain the rendered definition by The Benishangul-Gumuz Regional State technic vocation and enterprises development loan guarantee and Fund , issued with the Regional council regulation No. 69/2011

**Article 20.** **<u>Taxable Business Income</u>**

1/ The taxable business income of a taxpayer for a tax year shall be the total business income of the taxpayer for the year reduced by the total deductions Allowed to the taxpayer for the year.

